በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት



የገንዘብ ቢሮ

የመንግስት ንብረትን በሽያጭ ለማስወገድ የሚውል መደበኛ የጨረታ ሰነድ

ባህር ዳር

ሐምሌ/2018 **ዓ.ም**

መቅድም

የክልሉ የመንግስት መስሪያቤቶች ንብረቶችን በሽያጭ ማስወገድ የሚችሉት በመንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 306/2018 ፣ በክልሉ መንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 145/2018 አንዲሁም ለዚሁ ዓላማ ተብሎ በተዘጋጀው በዚሁ መደበኛ የጨረታ ሰነድ መሠረት ይሆናል፡፡

ይህ መደበኛ የጨረታ ሰነድ በገንዘብ ቢሮ የተዘጋጀ ሲሆን ዓላማውም የክልሉ መንግስት መስሪያ ቤቶች በሽያጭ እንዲወገዱ የወሰኗቸውን ንብረቶች በሽያጭ ለማስወገድ በሚወስኑበት ጊዜ በዋነኛነት በገዥና በሻጭ መካከል ሊፈጠሩ የሚችሉ አለመግባባቶችን በቀላሉ ለመፍታት እንዲያስችል ፣ የአወጋገድ ስርዓቱ ዘመናዊ፣ ግልፅ እና ከአድሎ የነፃ እንዲሆን ፣ ፍትኃዊ የንብረት አወጋገድ ሥርዓት እንዲሰፍን ለማድረግ ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡

ማውጫ

ክፍል እንድ ተጫራቾች ስለመጋበዝ 1
1. በሀራጅ ስለሚደረግ ሽያጭ 1
ክፍል ሁለት 2
የተጫራቾች መመሪያ 2
2..1 ስለ ተጫራቾች ብቃት ወይም ከተጫራቾች ስለሚጠበቅ ሁኔታ 2
2.2 ከጨረታው ጋር ተያይዞ ስላሉ ወጪዎች 3
2.3 የጨረታ ሰነድ 3
2.4 በጨረታ ሰነዱ ላይ ስለሚሰጥ ማብራሪያ 4
2.5 የጨረታ ሰነድ ስለማስተካከል 5
2.6 የጨረታ መነሻ ዋጋ 5
2.7 የጨረታ ማስከበሪያ 6
2.8 የውል ማስከበሪያ 7
2.9 ጨረታ ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ 8
2.10 ለጨረታ የቀረቡ ንብረቶችን ለተጫራቾች ስለማሳየት 9
2.11 ስለ ዋጋ አቀራረብ 9
2.12 የጨረታ ሰነድ ማቅረቢያ የመጨረሻ ቀን 9
2.13 የጨረታ ሰነድ ስለማስተካከል 10
2.14 ከጨረታ ስለመውጣት 10
2.15 ስለጨረታ አከፋፈት 10
2.16 ጨረታ ግምገማና ውድድር 10
2.17 አሸናፊውን የማሳወቂያ መስፈርት 11
2.18 አሸናፊውን ስለማሳወቅ 11
2.19 ከሻጭ መስሪያ ቤት ጋር ስለሚኖር ግንኙነት 12
ክፍል 3 12
አጭበርባሪነት፣ሙስና እና አቤቱታ የሚታይበት ሥርዓት 12
3.1 የማጭበርበርና የብልሹ አሰራር ድርጊት 12
3.2 አቤቱታ የሚታይበት ሥርዓት 13
ክፍል አራት 14
የጨረታ ማቅረቢያ እና የውል ስምምነት ቅፆች 14
4.1 የጨረታ ማቅረቢያ ቅፅ 14
4.2. የሚሸጡ እቃዎች ዝርዝር መግለጫ 15
4.3 የውል ስምምነት ቅፅ 16

ክፍል እንድ ተጫራቾች ስለመጋበዝ

1. በሀራጅ ስለሚደረግ ሽያጭ

ሀ) የመንግስት መ/ቤቶች ንብረቶቻቸውን በሃራጅ ለማስወገድ ሲወስኑ የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ስርዓትን ተጠቅመው ወይም ኤሌክትሮኒክ ባልሆነ ሥርዓት በሀራጅ ማስታወቂያቸው ላይ ቀጥሎ የተመለከቱትን ዝርዝሮች ማካተት አለባቸው፡፡

I. የመንግስት መ/ቤቱን ስምና አድራሻ፣

II. የዕቃዎችን ብዛት እና አይነት በሚመለከት አጠቃላይ መግለጫ፣

III. ማስያዝ ያለባቸው የጨረታ ማስከበሪያ አይነትና መጠን

IV. እቃዎች ለዕይታ ክፍት ሆኖ የሚቆዩበት ጊዜ እና የሚገኙበት ቦታ፣

V. የእቃዎች ዝርዝር የሚገኙበትን ቦታ ፣

VI. የሀራጅ ሽያጩ የሚከፈትበት ቀንና ሠዓት

VII. የሀራጁን ዙር ወይም ሀራጅ የሚቆይበት የጊዜ ገደብ እንዲሁም የሚጨመርበት የገንዘብ መጠን መቶኛ፣

VIII. ክፍያ ሚፈፀምበትን ጊዜ፣

IX. የመንግስት መ/ቤቱ ማናቸውንም ጨረታ ሙሉ በሙሉ ለመቀበል ወይም ላለመቀበል የሚችል መሆኑን እና በማናቸውም ጊዜ ሊሰርዘው እንደሚችል በግልጽ መጥቀስ፣

ለ) በግልፅ ጨረታ ስለሚደረግ ሽያጭ

የመንግስት መ/ቤቶች ንብረቶቻቸውን በጨረታ ለማስወገድ ሲወስኑ የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ስርዓትን ወይም ኤሌክትሮኒክ ያልሆነ ሥርዓትን ተጠቅመው ማስታወቂያቸው ላይ ቀጥሎ የተመለከቱትን ዝርዝሮች ማካተት አለባቸው፡፡

i. የመንግስት መ/ቤቱን ስምና አድራሻ፣

ii. የእቃዎችን አይነትና ዝርዝር ብዛት በሚመለከት አጠቃላይ መግለጫ

iii. ማስያዝ ያለባቸው የጨረታ ማስከበሪያ አይነትና መጠን

iv. እቃዎች ለዕይታ ክፍት ሆኖ የሚቆዩበት ጊዜ እና የሚገኙበት የእቃዎችን ወይም የንብረቱን ዝርዝር ከየት ማግኘት እንደሚቻል፣

v. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የሚሞሉበትን የጊዜ ገደብ

vi. ጨረታ የሚዘጋበትና የሚከፈትበት ቀንና ሠዓት

vii. ጨረታዎች በሲስተሙ መላክ የሚችሉበት የመጨረሻ ቀን

viii. የጨረታ ማስከበሪያውን መጠንና ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ተጫራቾች ከውድድሩ ቢወጡ የጨረታ ማስከበሪያውን ለመንግስት ገቢ እንደሚሆን የሚገልፅ ሀሳብ ፣

ix. የጨረታ አሸናፊው ክፍያውን የሚፈፅምበት ጊዜ፤

x. የጨረታ አሸናፊው ክፍያውን ፈፅሞ ንብረቱን ሙሉ በሙሉ የሚያነሳበት ጊዜ መገለጽ አለበት፣

xi. የመንግስት መ/ቤቱ ማናቸውንም ጨረታ ለመቀበል ወይም ላለመቀበል እንደሚችልና በቂ ምክንያት ሲኖረው በማናቸውም ጊዜ ጨረታውን እንደሚሰርዝ፣

xii. ተቋማት በራሳቸው በሚያስወግዱበት ወቅት ተጫራቾች እንዲጫረቱ የሚሰጠው ጊዜ ከ15 ቀናት ያላንሰና በማዕከል በሚወገድበት ወቅት ከ20 ቀናት ያላንሰ መሆኑን፤

xiii. የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በሚጠየቀው መሰረት እንዲያቀርብ፤

ክፍል ሁለት

የተጫራቾች መመሪያ

2..1 ስለ ተጫራቾች ብቃት ወይም ከተጫራቾች ስለሚጠበቅ ሁኔታ፤

2.1.1 ይህ ጨረታ ማናቸውም ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው ወይም በኢትዮጵያ ወይም በክልሉ ህግ መሰረት የተቋቋመ የንግድ ደርጅት፣

2.1.2 በኢትዮጵያ ህግ መሰረት የተቋቋመ የንግድ ደርጅት ተጫራች ከሆነ ህጋዊነቱን የሚያሳዩ ሰነዶች (በዘመኑ የታደሰ ንግድ ፈቃድ፣ የታክስ ምዝገባ እና የታክስ ከፋይነት ሰርተፍኬት) ማቅረብ ይጠበቅበታል፣

2.1.3 ዕሴት በመጨመር መልሶ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ በሽያጭ ለሚወገዱ ንብረቶች ተጫራቾች በዘርፉ የተሰማሩ መሆናቸውን ማርጋገጫ ማቅርብ ይኖርበታል፡፡

2.2 ከጨረታው ጋር ተያይዞ ስላሉ ወጪዎች፤

2.2.1 ማንኛውም ከጨረታው ጋር ተያያዥ የሆኑ ወጪዎች ለምሳሌ፡ የማስታወቂያ ወጪ ፣ የፅህፈት መሳሪያ ወጪ፣ የሠራተኞች አበል የመሳሰሉት በሻጭ መስሪያ ቤት የሚሸፈኑ ይሆናል፡፡

2.2.2 ለጨረታ ሠነድ ዝግጅት የሚያወጣውን ወጪ መተኪያ መጠየቅ አለበት፡፡

2.2.3 ንብረትን በሽያጭ የሚያስወግደው የመንግስት መስሪያ ቤት እንደ አስፈላጊነቱ ለጨረታ ሰነዱ ከብር 200 (ሁለት መቶ ብር) ያላነሰ እና ከብር 500 (አምስት መቶ ብር) ያልበለጠ ክፍያ ሊጠይቅ ይችላል::

2.2.4 በማዕከል የሚሸጡ ንብረቶች ሲሆኑ ከብር 500 (አምስት መቶ ብር) ያላነሰ እና ከብር 2000 (ሁለት ሺህ ብር) ያልበለጠ ክፍያ ሊጠይቅ ይችላል::

2.2.5 የሚወገደው ንብረት ቀደም ብሎ ያልተከፈሉ የተሸከርካሪ የስም ማዘዋወሪያና ቦሎ ክፍያ ውጪ ያልተከፈለ ዕዳ ካለበት የመንግሥት መስሪያ ቤቱ የመሸፈን ኃላፊነት እንደሌለበት መገለፅ አለበት፡፡

2.3 የጨረታ ሰነድ

2.3.1 የጨረታ ሰነዱ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሁሉ ሊያሟላ ይገባል፤

I. የጨረታው ማስታወቂያ፤
II. ስለተጫራቾች መመሪያ፣
III. የሚወገዱ ንብረቶች አይነትና የጨረታ መነሻ ዋጋ፣
IV. ከተጫራቾች ስለሚጠበቅ ሁኔታ፤

V. ለጨረታ የሚያስፈልጉ ቅፆችን፤

VI. የዋጋ ማቅረቢያ ቅፆችን፤

VII. በገዥ እና በሻጭ መካከል ስለሚኖር መብትና ግዴታ፤

2.4 በጨረታ ሰነዱ ላይ ስለሚሰጥ ማብራሪያ፤

2.4.1 ማንኛውም ተጫራች በጨረታ ሰነዱ ላይ ሊብራራለት የሚፈልገው ነገር በሚኖርበት ጊዜ ጨረታው ከመዘጋቱ 5 ቀን በፊት የኤሌክሮኒክ ስርዓቱን ወይም ኤሌክትሮኒክ ባልሆነ ዘዴ በመጠቀም ሻጭ መስሪያ ቤትን መጠየቅ የሚችል ሲሆን ሻጭ መስሪያ ቤትም በእርግጥም ማብራሪያ ያስፈልገዋል ብሎ ሲያምን የተስተካከለውን ማብራሪያ ሁሉም ተጫራቾች እንዲያውቁት ምላሽን የኤሌክሮኒክ ስርዓቱን በመጠቀም ወይም ኤሌክትሮኒክ ባልሆነ ዘዴ በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

2.4.2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2.4.1 ላይ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ የማብራሪያ ወይም የማሻሻያ ጥያቄ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች ሲቀርብ መ/ቤቱ ጨረታውን ከመክፈቱ በፊት በ3 የሥራ ቀናት ውስጥ ምላሹን የጨረታ ሰነዱ ተደራሽ በተደረገበት ሥርዓት ማውጣት አለበት፡፡

2.4.3 የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የጨረታ ሰነዱን ይዘት ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው እና በማሻሻያው የተመለከቱ ማስተካከያዎችን ለማድረግ በቂ ጊዜ የሌለ መሆኑን ሲረዳ የጨረታ ሰነዱን ለገዙና በቀጣይ ለሚገዙ ተጫራቾች ሁሉ በእኩል ጊዜ የተስተካከለው የጨረታ ሰነድ እንዲደርሳቸው መደረግ አለበት፡፡ የመጫረቻ ሰነዳቸውን አሻሽለው ለማዘጋጀት በቂ ጊዜ እንዲኖራቸው ለማድረግም የጨረታ ማቅረቢያ ጊዜውን ቢያንስ ለ5 (አምስት) ተጨማሪ የሥራ ቀናት ማራዘም አለበት ፡፡

2.4.4 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2.4.3 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የተሻሻለውን የጨረታ ሰነድ የጨረታ ማስታወቂያ በወጣበት በመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት ወይም በጋዜጣ ወይም በሌሎች መገናኛ ዘዴዎች እና በመ/ቤቱ ድረ-ገጽ ላይ የጨረታ መዝጊያ ቀኑን ማራዘም አለባቸው፡

2.4.5 መስሪያቤቱ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን በመስሪያቤቱ በተዘጋጀ የጨረታ ሰነድ ላይ የጨረታ ሰነድ የገዙትን ተጫራቾች በሙሉ ማብራሪያና ማሻሻያ ገለፃና ውይይት ለማድረግ ሊጠራ ይችላል፡፡ የሚደረገው ውይይትም በቃለ-ጉባኤ መያዝ አለበት፡፡

2.5 የጨረታ ሰነድ ስለማስተካከል፤

2.5.1 ሻጭ መስሪያ ቤት የጨረታ ሰነዱ መስተካከል አለበት ብሎ ሲያምን ጨረታው ከመዘጋቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ የጨረታ ሰነዱን ማስተካከል ይችላል፡፡

2.5.2 ሻጭ መስሪያ ቤት የተስተካከለውን የጨረታ ሰነድ ሁሉም ዕጩ ተወዳዳሪዎች እንዲያውቁት የኤሌክሮኒክ ስርዓቱን በመጠቀም ወይም ኤሌክትሮኒክ ባልሆነ ዘዴ በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

2.5.3 ሻጭ መስሪያ ቤት የተስተካከለውን የጨረታ ሰነድ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች በድጋሚ በሚያሳውቅበት ጊዜ ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን አንብበው የመጫረቻ ሰነዳቸውን እንዲያቀርቡ በቂ ጊዜ መስጠት ይኖርበታል፡፡የመጫረቻ ሰነዳቸውን አሻሽለው ለማዘጋጀት በቂ ጊዜ እንዲኖራቸው ለማድረግም የጨረታ ማቅረቢያ ጊዜውን ቢያንስ ለ5 (አምስት) ተጨማሪ የሥራ ቀናት ማራዘም አለበት

2.6 የጨረታ መነሻ ዋጋ፤

2.6.1 ሻጭ መስሪያ ቤት ስለእያንዳንዱ ሊወገድ ስለቀረበ ዕቃ ዓይነት ፣ የነጠላ የጨረታ ***መነሻ ዋጋ*** በግልፅ በጨረታ ሰነዱ ላይ ማመላከት አለበት፡፡

2.6.2 ተጫራቾች በተቀመጠው መነሻ ዋጋ እና ከዚያ በላይ በሆነ ዋጋ ብቻ መወዳደር ያለባቸው ሲሆን ከተቀመጠው የጨረታ መነሻ ዋጋ በታች ቢያቀርቡ ከጨረታ ውድቅ መደረግ አለባቸው፡፡

2.6.3 በጨረታ ወይም በሀራጅ ንብረቱን ለመሸጥ የተደረገው ጥረት ውጤታማ ካልሆነ ንብረቱ የሚወገድበትን ሌላ አማራጭ የማስወገጃ ዘዴ ለበላይ ኃላፊው ቀርቦ መወሰን አለበት፣

2.6.4 የሚሸጠው ንብረት አዋጭነቱን በማየት በነጠላ ወይም በጥቅል ጨረታ ማውጣት ይችላል፡፡

2.6.5 በጨረታው አንደኛ የወጣው ተጫራች ዕቃውን ለመረከብ ፈቃደኛ ካልሆነ ያስያዘውን የጨረታ ማስከበሪያ በመውረስ መስሪያ ቤቱ በቅድሚያ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ በመገምገም፣እንዲሁም የዋጋ ቅናሽ ልዩነቱ ወቅታዊ እና አዋጭ መሆኑን በማረጋገጥ በውድድሩ ሁለተኛ የወጣውን ተጫራች አሸናፊ ማድረግ የሚቻል ሲሆን ዕቃውን ለመረከብ ፈቃደኛ ካልሆነ ያስያዘውን የጨረታ ማስከበሪያ በመውረስ አዲስ ጨረታ ማውጣት ይችላል፡፡

2.7 የጨረታ ማስከበሪያ ፤

2.7.1 ማናቸውም ተጫራች ሻጭ መስሪያ ቤት ያስቀመጠውን መጠን ያህል የጨረታ ማስከበሪያ ለማስያዝ በተዘረጋው የኤሌክትሮኒክ ወይም ኤሌክትሮኒክ ባልሆነ ስርዓት መስረት ማስያዝ ይኖርበታል፡፡

2.7.2 የሚወገዱ ንብረቶችን ግምታዊ መነሻ ዋጋውን መሠረት በማድረግ ከ0.5% ያላነሰና ከ2% ያልበለጠ የጨረታ ማስከበሪያ በገንዘብ ተወስኖ መጠየቅ አለበት፡፡ ሆኖም በዚህ አግባብ የሚጠየቀው የጨረታ ማስከበሪያ መጠን በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ ዋስትና ከብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ) ሊበልጥ አይገባም፡፡

2.7.3 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2.7.2 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የሚያስወግዳቸው ተሽከርካሪ እና ማሽነሪ በሚሆኑበት ጊዜ ከመነሻ ግምታዊ ዋጋ ከ5% እስከ 10% ድረስ የጨረታ ማስከበሪያ በገንዘብ ተወስኖ መጠየቅ ይቻላል፡፡ ሆኖም በዚህ አግባብ የሚጠየቀው የጨረታ ማስከበሪያ መጠን በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ ዋስትና ከብር 500,000 (አምስት መቶ ሺህ) ሊበልጥ አይገባም፡፡

2.7.4 የሐራጅ ጨረታ ላይ የሚሳተፍ ማንኛውም ተጫራች የጨረታ ማስከበሪያ በጥሬ ገንዘብ ወይም የክፍያ ትዕዛዝ ማረጋገጫ/በሲ.ፒ.ኦ/ ለመስሪያ ቤቱ ገቢ አድርጎ ደረሰኝ ማቅረብ አለበት፡፡

2.7.5 ጨረታው ከተራዘመ ተጫራቹ የስያዘውን የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ማራዘም ይኖርበታል፡

2.7.6 የንብረት አስተዳደር የስራ ክፍል እያንዳንዱ ሽያጭ የተያዘውን የጨረታ ማስከበሪያ በጨረታው ያሸነፈው ተጫራች እንደተመረጠ እና ቅሬታ የማቅረቢያ ጊዜ ሲጠናቀቅ ጨረታውን ላላሸነፉ ተጫራቾች መመለስ አለበት፣

2.7.7 ማናቸውም ተጫራች የጨረታ መክፈቻ የግል የሚስጥር ቁልፍ ከላከ በኋላ ወይም ኤሎክትሮኒክ ባልሆነ ስርአት የጨረታ ሳጥን ከተዘጋ በኃላ በራሱ ፈቃድ ከጨረታው ቢወጣ ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዘው ገንዘብ ተወርሶ ለመንግስት ገቢ ይሆናል፡፡

2.7.8 ማናቸውም ተጫራች ከተጫረተ በኋላ በሌሎች ተጫራቾች ተበልጦ ቢሸነፍ ከ5 የሥራ ቀናት በኋላ ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዘው ገንዘብ ይመለስለታል፡፡

2.7.9 አሸናፊ የሆነው ተጫራች ያሸነፈበትን ንብረት በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ውል ለመውሰድ ፍቃደኛ ካልሆነ ያስያዘው የጨረታ ማስከበሪያ የሚወረስ ይሆናል፡፡

2.8 የውል ማስከበሪያ

2.8.1 ማናቸውም አሸናፊ ተጫራች ያሸነፈ እንደሆነ ያሸነፈባቸውን ዕቃዎች ሙሉ ክፍያ ከፍሎ እስከሚወስድ ድረስ ለውል ዋስትና የሚሆን የተሸጠውን ንብረት ጠቅላላ ዋጋ 10% (አስር በመቶ) ያላነሰ ማስያዝ አለበት፡፡ሆኖም መ/ቤቱ ጥቃቅን ሽያጮች ሆነው አስቀድሞ ክፍያ የሚፈፀምባቸው ከሆነ ውልና የውል ማስከበሪያ ሳይጠየቅ ሽያጩን መፈፀም ይችላል፡፡

2.8.2 በማእከል በሽያጭ የማስወገድ ስራ ሲከናወን የውል ማስከበሪያ አያስፈልግም ብሎ ቢሮው ካመነ የውል ማስከበሪያ ሳይጠየቅ ውል በመውሰድ ማስወገድ ይችላል፡፡

2.8.3 ከአቅም በላይ የሆነ አስገዳጅ ሁኔታ መኖሩ ተረጋግጦ እና በመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ተፈቅዶ በውሉ በልዩ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር አሸናፊው ድርጅት ውል ከገባበት ቀን ጀምሮ በ10 (አስር) የስራ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ሙሉ ክፍያ ከፍሎ ንብረቱን ማንሳት አለበት፡፡

2.8.4 ሆኖም ተጫራቹ ላሸነፈበት ዕቃ ሙሉ ክፍያ ከፍሎ ነገር ግን እቃውን በ10 (አስር) የስራ ቀናት ውስጥ ካላነሳ ከ10ኛው ቀን በኃላ ላላነሳበት በውል ቀን በየቀኑ ብር 500.00 /አምስት መቶ ብር/ ቅጣት መክፈል አለበት፡፡

2.8.5 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2.8.4 የተደነገገው ተግባራዊ እየሆነ ተጫራቹ ተጫርቶ ያሸነፈበትን ዕቃ እስከ አንድ ወር የማያነሳ ከሆነ ዕቃውን እንደማይፈልገው ተቆጥሮ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የውል ማስከበሪያው ተወርሶ ዕቃው እንደገና ለህዝብ በጨረታ ይሸጣል፡፡

2.8.6 ከላይ በንዕስ አንቀጽ 2.8.5 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የአንድ ወር ቅጣቱ ተደምሮ ከተቆረጠ በኋላ ቀሪው ገንዘብ ለአሸነፊው ተመላሽ መደረግ አለበት፡፡

2.9 ጨረታ ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ

2.9.1 ጨረታው ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ በሻጭ መስሪያ ቤት የሚወሰን ሆኖ መስሪያ ቤቱ በጨረታው የቀረቡ ሰነዶችን ገምግሞ አሸናፊውን ለመለየት የሚወስደውን ጊዜ ታሳቢ ያደረገ ይሆናል፡፡

2.9.2 ጨረታው ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ሻጭ መስሪያ ቤት እንደአስፈላጊነቱ ሊያራዝመው ይችላል፡፡

2.9.3 መስሪያቤቶች የመጫረቻ ሰነዱ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ እና ከአሸናፊው ድርጅት ጋር ውል መፈራረም አለባቸው፡፡ ሆኖም ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች ሂደቱ ሳይጠናቀቅ ለሽያጩ የቀረበው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ የሚያበቃ መሆኑን መ/ቤቱ ሲረዳ ዋጋቸው ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ለተጨማሪ ቀናት እንዲያራዝሙለት መጠየቅ አለበት፡፡

2.9.4 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 2.9.3 በተመለከተው መሰረት ተጫራቾች አንዲያራዝሙ የሚጠየቁት ተጨማሪ ቀናት መ/ቤቱ የቀረውን የሽያጭ ሂደት ለማጠናቀቅ የሚበቃውን ያህል ቀናት ብቻ መሆን አለበት፡፡ ሆኖም ተጫራቾች በማንኛውም ምክንያት ዋጋቸው ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ለማራዘም ፈቃደኛ ባይሆኑ ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዙትን ዋስትና መውረስ ሳያስፈልግ ከጨረታው ውድድር እንዲወጡ ይደረጋል፡፡

2.9.5 ዋጋቸው ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ የማሻሻል የቀረበላቸውን ጥያቄ የተቀበሉ ተጫራቾች ጥያቄውን መቀበላቸውን እና የመቆያ ጊዜውን ያራዘሙት እስከመቼ እንደሆነ በመጥቀስ በጽሑፍ ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም ለዚህ ጨረታ ያስያዙት የጨረታ ዋስትና መቆያ ጊዜ ማሻሻል ወይም አዲስ ዋስትና ማቅረብ አለባቸው፡፡

2.9.6 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 2.9.5 በተገለጸው መሰረት የጨረታ ዋስትናውን ፀንቶ መቆያ ጊዜ ያላሻሻለ ተጫራች ያቀረበው የጨረታ ዋስትና ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ለማሻሻል ፈቃደኛ እንዳልሆነ ተቆጥሮ ከጨረታው ውድድር ውጭ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

2.10 ለጨረታ የቀረቡ ንብረቶችን ለተጫራቾች ስለማሳየት፤

2.10.1 ባለ ንብረት መስሪያ ቤት ወይም ሻጩ መስሪያ ቤት ጨረታው አየር ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ ጨረታው እስከሚዘጋበት ጊዜ ድረስ ለጨረታ የቀረቡ ንብረቶችን ለተጫራቾች በግልፅ ማሳየት ይኖርበታል፡፡

2.11 ስለ ዋጋ አቀራረብ

2.11.1 ማንኛውም ተጫራች የዋጋ ማቅረቢያ ሰነዱን በተዘጋጀው የኤሌትሮኒክ ስርዓት ወይም ኤሌክትሮኒክ ባልሆነ ዘዴ መሰረት ለሻጭ መስሪያ ቤት መላክ ይኖርበታል፡፡

2.11.2 በሀራጅ ከሚሸጥ ንብረት በስተቀር ማንኛውም ተጫራች ሌሎች ተጫራቾች በሰጡት ዋጋ ላይ በመንተራስ ዋጋ ማቅረብ አይችልም፡፡

2.11.3 ተጫራቹ ያቀረበው የዋጋ ማቅረቢያ ሲታይ ግልፅነት የጎደለው እና የሚያሻማ ሆን ተብሎ ለማጭበርበር ታስቦ የተዘጋጀ መሆኑን ሻጭ መስሪያ ቤት ካረጋገጠ የተጫራቹን ዋጋ ማቅረቢያ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ውድቅ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

2.11.4 ጨረታው ከተዘጋ በኋላ የሚቀርብ የጨረታ ዋጋ ተቀባይነት የለውም፡፡

2.12 የጨረታ ሰነድ ማቅረቢያ የመጨረሻ ቀን

2.12.1 ሻጭ መስሪያ ቤት ጨረታው የሚዘጋበትን ቀን እና ሠዓት በጨረታ ሰነዱ ላይ በግልጽ ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡

2.12.2 ሻጭ መስሪያ ቤት እንደ አስፈላጊነቱ ጨረታው የሚዘጋበትን ጊዜ ሊያራዝም ይችላል፡፡ ሆኖም ለሁሉም ተጫራቾች ጨረታው የሚዘጋበት ጊዜ የተራዘመ ስለመሆኑ በኤሌክተሮኒክ ስርዓት መሰረት ወይም ኤሌክትሮኒክ ባልሆነ ስርአት በወጣበት ጋዜጣ ወይም ማስታወቅያ ማሳወቅ አለበት፡፡

2.13 የጨረታ ሰነድ ስለማስተካከል

2.13.1 ማናቸውም ተጫራች ዕቃውን ለመግዛት ያቀረበውን የመጫረቻ ሰነድ ማስተካከል ቢፈልግ ጨረታው ከመዘጋቱ በፊት የኤሌክትሮኒክ ስርዓቱን ተጠቅሞ ወይም ኤሌክትሮኒክ ባልሆነ መንገድ የተስተካከለውን ሰነድ መላክ ይኖርበታል፡፡

2.14 ከጨረታ ስለመውጣት

2.14.1 ማንኛውም ከጨረታ ለመውጣት የሚፈልግ ተጫራች ጨረታው ከመዘጋቱ በፊት ከጨረታው ሊወጣ ይችላል፡፡

2.14.2 ማንኛውም ተጫራች በጨረታ መክፈቻ ወቅት የጨረታ መክፈቻ የግል የሚስጥር ቁልፍ እስካልላከ ድረስ ከጨረታው እራሱን እንዳገለለ ይቆጠራል፡፡

2.14.3 ከላይ በንዑስ አንቀፅ 2.14.1 እና 2.14.2 መሰረት ከጨረታ የሚወጣ ተጫራች ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዘው ገንዘብ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ይመለስለታል፡፡

2.14.4 ማንኛውም ጨረታው ከተዘጋ በኋላ የሚቀርብ ከጨረታ የመውጣት ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

2.15 ስለጨረታ አከፋፈት

2.15.1 ሻጭ መስሪያ ቤት በጨረታ ሰነዱ በተገለፀው ቀንና ሰዓት መሠረት ጨረታውን መክፈት ይኖርበታል፡፡

2.15.2 ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ሻጭ መስሪያ ቤት እያንዳንዱን የተጫራቹን ስም እና ተጫራቾቹ ለእያንዳንዱ ለተወዳደሩበት ዕቃ ያቀረቡትን የመግዣ ዋጋ እንዲሳውቅ ይደረጋል ፡፡

2.15.3 ሻጭ መስሪያ ቤት ጨረታው በተከፈተበት ዕለት የተከናወኑ ሁኔታዎችን የሚያሳይ ቃለ ጉባዔ መያዝ ይኖርበታል፡፡

2.16 ጨረታ ግምገማና ውድድር

2.16.1 ሻጭ መስሪያ ቤት የቀረቡ የዋጋ ማቅረቢያዎች በአግባቡ በመመልከት ህጋዊ ያልሆኑ ተጫራቾችን ማለትም የጨረታ ማስከበሪያ ያላቀረቡትን እና የሚያሻማና ግልፅ ያልሆነ

እንዲሁም ለማጭበርበር ተግባር የቀረበን የዋጋ ማቅረቢያን በመለየት ተጫራቾችን ከጨረታ ማስወጣት ይኖርበታል፡፡

2.16.2 መስሪያ ቤቱ የጨረታ ሂደቱን ጨረታው ከተከፈተበት ጊዜ ጀምሮ ጨረታው ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ከማለፉ በፊት አሸናፊና ተሸናፊውን በመለየት ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

2.16.3 .ተጫራቾች ለአንድ ምድብ የተለያዩ ዕቃዎችን በጥቅል እና በነጠላ እኩል ዋጋ በመስጠት አሸናፊ ቢሆኑ እንደገና የዋጋ ማሻሻያ አድርገው እንዲወዳደሩ በማድረግ የተሻለ ዋጋ የሰጠው አሸናፊ ይሆናል፣ ሆኖም ድጋሚ ተመሳሳይ ዋጋ ከሰጡ አሸናፊው በዕጣ እንዲለይ ይደረጋል፡፡

2.17 አሸናፊውን የማሳወቂያ መስፈርት፤

2.17.1 ሻጭ መሰሪያ ቤት ለጨረታ ለቀረቡ ዕቃዎች ከቀረበው የዋጋ ማቅረቢያ መካከል ከፍተኛ ዋጋ ያቀረበውን ተጫራች ድርጅት /ግለሰብ/ በአሸናፊነት መምረጥ ይኖርበታል፡፡

2.18 አሸናፊውን ስለማሳወቅ፤

2.18.1 ሻጭ መስሪያ ቤት አሸናፊና ተሸናፊውን ከለየ በኋላ የአሸናፊዎችን ዝርዝር በቅደም ተከተላቸው መሰረት የኤሌክትሮኒክ ሥርዓት በመጠቀም ወይም ኤሌለክትሮኒክ ባልሆነ ዘዴ በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት፤

2.18.2 አሸናፊው ተጫራች ማሸነፉ ከተገለጸለት ቀን ጀምሮ ከ5 የስራ ቀናት በኃላ ባሉት 10 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ቀርቦ ውሉን መፈረም ይኖርበታል፡፡ጨረታውን ያወጣው መስሪያቤት ወይም በማዕከል ንበረት የሚያስወግድ አካል የጨረታውን ውጤት ለተጫራቾች ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ 5 የሥራ ቀናት ከመመሉቱ በፊት የሽያጭ ውል መፈረም የለበትም፡፡

2.18.3 አሸናፊው ተጫራች ያሸነፉበትን ንብረት ዋጋ ክፍያ በመፈፀም ደረሰኝ ማቅረብ አለበት፡፡

2.18.4 በጨረታው ማስታወቂያ ላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቀርቦ ክፍያውን ያላጠናቀቀ አሸናፊ ተጫራች ለጨረታ ዋስትና ያስያዘውን ገንዘብ ለመስሪያ ቤቱ ገቢ ሆኖ ከጨረታው ይሰረዛል፡፡

2.18.5 አሸናፊው ተጫራች ከሚረከበው ንብረት ውስጥ ጉድለት ቢገኝ ወይም ያሸነፈበትን ንብረት ሻጭ መስሪያ ቤት ሙሉ በሙሉ ሊያስረክበው ካልቻለ ጉዳዩን **በአምስት የስራ** ቀናት ውስጥ ለሻጭ መስሪያ ቤት የበላይ ሃላፊ ቅሬታወን ማቅረብና ውሳኔ ማግኘት አለበት፡፡ ሆኖም የሻጭ መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ እስከ **ሰባት የስራ ቀናት ውሳኔ** ካልሠጠው ወይም በተሰጠው ውሳኔ ካልረካ አቤቱታውን በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ ለመንግስት ግዥና ንብረት አወጋገድ ይግባኝ አጣሪና ውሳኔ ሰጪ ቦርድ በማቅረብ ውሳኔ ማግኘት ይችላል፡፡

2.19 ከሻጭ መስሪያ ቤት ጋር ስለሚኖር ግንኙነት፤

2.19.1 ማንኛውም ተጫራች አሸናፊና ተሸናፊ እስከሚለይበት ጊዜ ድረስ ከጨረታው ጋር በተያያዘ በመስሪያ ቤቱ ከሚሠራ ሠራተኛ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት ማድረግ አይቻልም፡፡

2.19.2 ተጫራቾች በማናቸውም የጨረታ ሂደት ላይ ወይም በውል አፈፃፀም ወቅት በሙስና ፣ በማጭበርበር ፣ በመመሳጠር ፣ በማስገደድና በማደናቀፍ ተግባር ተካፋይ መሆናቸው ከተረጋገጠ ተገቢው ህጋዊ እርምጃ ይወሰድባቸዋል፡

ክፍል 3

አጭበርባሪነት፣ሙስና እና አቤቱታ የሚታይበት ሥርዓት

3.1 የማጭበርበርና የብልሹ አሰራር ድርጊት

3.1.1 በአሸናፊነት የተመረጡ ተጫራቾች በራሳቸው ወይም በተወካያቸው አማካኝነት ጨረታውን ለማሸነፍ በማሰብ በሽያጭ ሂደቱ ውስጥ ከሚሳተፉ የሻጭ መስሪያ ቤት ሠራተኞች ጋር የብልሹ አሰራር፣ የማጭበርበር የማሴር፣ የማስገደድ ድርጊት በጨረታው ሒደት ወቅት ፈጽመው ከተገኙና ድርጊቱን መፈፀማቸው

3.1.2 ተጫራቾች በማናቸውም በጨረታ ሂደት ጊዜ ወይም በውል አፈፃፀም ወቅት በብልሹ አሰራር፣ በማጭበርበር፣ በመመሳጠር፣ በማስገደድና በማደናቀፍ ተግባር ተካፋይ መሆናቸው ከተረጋገጠ በህግ እንዲጠየቁ ይደረጋል፡፡

3.1.3 ተጫራቾች በብልሹ አሰራርና የማጭበርበር ድርጊት የማይፈፅሙ ስለመሆናቸው ከዚሁ የጨረታ ሰነድ ላይ በተያያዘው ቅፅ ላይ ማመልከት ይኖርባቸዋል፡፡

3.2 አቤቱታ የሚታይበት ሥርዓት

3.2.1 በንብረት ሽያጭ አፈፃፀም ቅር የተሰኘ ተጫራች ለአቤቱታው መሰረት የሆነው የመጨረሻ ውሳኔ ካወቀበት ወይም ማወቅ ይገባው ከነበረበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር በተከታታይ 5/አምስት/ የስራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን በቅድሚያ ማቅረብ ያለበት ለሽያጭ ፈፃሚው መስሪያ ቤት የበላይ ሀላፊ ይሆናል ፡፡

3.2.2 የሽያጭ ፈፃሚው መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ **በሰባት የስራ ቀናት** ውስጥ አቤቱታውን አጣርቶ ውሳኔ መሰጠት አለበት፡፡

3.2.3 ሆኖም የሻጭ መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ውሳኔ ካልሠጠው አቤቱታውን ለመንግስት ግዥና ንበረት አወጋገድ አቤቱታ አጣሪና ውሳኔ ሰጪ ቦርድ በማቅረብ ውሳኔ ማግኘት ይችላል፡፡

3.2.4 ቦርዱ የሚሰጠው ውሳኔ በሁለቱም አካላት ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

ክፍል አራት

የጨረታ ማቅረቢያ እና የውል ስምምነት ቅፆች

4.1 የጨረታ ማቅረቢያ ቅፅ

የሻጭ መሰሪያ ቤት ስም ----------

የጨረታ ሰነድ የወጣበት ቀን----------

(የሽያጭ አወጋገድ) ዘዴ----------

የሽያጭ መለያ ቁጥር ----------

እኛ ከታች የፈረምነው ተጫራቾች / ተወዳዳሪዎች ከላይ የተጠቀሰውን የሽያጭ መለያ ቁጥር ----------የጨረታ ሰነዱን በተመለከተ የሚከተለውን እናረጋግጣለን ፡፡

የጨረታ ሰነዱን መርምረን ሁሉንም ያለምንም ተቃውሞ ተቀብለናል፡፡

በጨረታ ሰነዱ ውስጥ ለሽያጭ የተዘረዘሩትን ዕቃዎች የመውሰጃ ጊዜ ከጨረታ ሰነዶች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ እናቀርባለን ፡፡

ጨረታው ፀንቶ የሚቆየው በጨረታ ሰነዱ በተጠቀሰው የጨረታ ማቅረቢያው ማብቂያ የጊዜ ገደብ ከመጠናቀቁ በፊት የሚቀርብ የጨረታ ሠነድ ተቀባይነት ይኖረዋል ፡፡

የቀናቶች ብዛት ----------

ስም ----------በጨረታ ሰነዱ ላይ የሚፈርም ግለሰብ ሙሉ ስም ይግባ፡፡

ኃላፊነት ----------

የፈራሚው ግለሰብ ህጋዊ አግባብነቱ የተመለከተው ግለሰብ ፊርማ ----------

-የተጫራቾች ሙሉ ስም ይግባ ----------

ቀን፡ ----------፣ ወር---------- የተፈረመበት ዓ.ም ----------

ሙሉ አድራሻ ----------

የስልክ ቁጥር----------

4.2. የሚሸጡ እቃዎች ዝርዝር መግለጫ

የሽያጭ መለያ ቁጥር----------

የሎት ቁጥር----------

የሎት ስም----------

ምድብ	የዕቃው ዓይነት	የዕቃው ብዛት	የጨረታ ግምታዊ መነሻ ነጠላ ዋጋ/	ተጫራቾች የሰጡት ዋጋ	
				በአሀዝ	በፊደል

<u>ማሳሰቢያ</u>

- ✓ **ተጫራቾች በዚህ ጥቅል የተጠቀሱትን እቃዎች በሙሉ መጫራት የሚችሉ ሲሆን በጥቅል የሚወዳደሩበትን ዋጋ መጥቀስ ይኖርባቸዋል**
- ✓ **ተጫራቾች በሚሰጡት ዋጋ ላይ ስርዝ ድልዝ ካለው ተቀባይነት አይኖረውም**

ስም----------

ፊርማ----------

ቀን----------

4.3 የውል ስምምነት ቅፅ

የሽያጭ የሚፈፅመው -ዕቃው አይነት ----------

የሽያጭ መለያ ቁጥር፤----------

ይህ ውል ዛሬ----------ወር ----------ቀን ---------ዓ.ም ከዚህ በኋላ ገዥ እየተባሉ የሚጠሩ ---------- --በሌላ በኩል በመሆን

- ✓ **ሽያጭ ፈፃሚው አካል የተወሰኑ ዕቃዎችን (ዕቃዎቹ አጭር መግለጫ ይግባ)----------**

- ✓ **-ከዚህ በኋላ ዕቃዎች እየተባሉ የሚጠሩ ---------- ለመሸጥ ጨረታ አውጥቶ ሻጩ ያቀረበው ጠቅላላ ዋጋ ----------የውል ዋጋ በፊደል---------- በአሃዝ ----------**
- ✓ **-ከዚህ በታች የውል ዋጋ እየተባለ የሚጠራ ----------**

ሁለቱ ወገኖች እንደሚከተለው ተዋውለዋል

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሰነዶች በሻጭና በገዥ መካከል የመጨረሻ ፈራሚ ከፈረመበት ቀን ጀምሮ ስራ ላይ ይውላል::

ዕቃው የሚገኝበት ቦታ----------

የዕቃዎች ዝርዝርና የእያንዳንዱ ዋጋ----------

ክፍያው የሚፈፀምበት ቀን

ፊርማ ----------የሽያጭ ፈፃሚ መ/ቤት ስም----------

ስለሻጭ ፈፃሚው አካል

-የሽያጭ ፈፃሚ መ/ቤት ስም ----------

አግባብ ያለው ተወካይ ስም----------

ኃላፊነት----------

ፊርማ---------- ቀን ----------

ስለ ገዥው

የገዥው ስም ----------

ፊርማ----------

ሕጋዊ ውክልና ያለው ተወካይ ስም----------

ኃላፊነት----------

ቀን----------

ምስክሮች

የሽያጭ ፈፃሚ አካል ስም ----------ፊርማ----------

የምስክር ስም ----------ፊርማ----------

ኣላፊነት----------

ቀን----------

የገዥ ስም ----------ፊርማ----------

የምስክር ስም ----------ፊርማ

ኣላፊነት----------

ቀን----------

ለሽያጭ የተዘጋጁ ልዩ ልዩ ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች የዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ

የ----------መ/ቤት የተሸከርካዎች ዝርዝር

ተሽከርካሪዎቹ የሚገኙበት ቦታ ፡- ---------- በሚገኘው የተቋሙ ግቢ ውስጥ

ተ.ቁ	የተሸከርካሪው አይነት	የተሸከርካሪው ኮድ	ሞዴል	የሞተር ቁጥር	የሻንሲ ቁጥር	የጨረታ መነሻ ዋጋ	ተጫራቹ የሰጠው ዋጋ	
							በአሃዝ	በፊደል

የተጫራቹ ሙሉ ስም---------- ፊርማ---------- ቀን----------

ለሽያጭ የተዘጋጁ ልዩ ልዩ ያገለገሉ ንብረቶች የዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ

የ----------መ/ቤት የሚወገዱ ንብረቶች ዝርዝር

ተ.ቁ	የእቃው አይነት	መለያ ኮድ	መለኪያ	ብዛት	የጨረታ መነሻ ዋጋ	ተጫራቹ የሰጠው ዋጋ	
						በአሀዝ	በፊደል

ንብረቱ የመገኝበት ቦታ----------